# ሥነ ምግባር ሲሉ. . .

ስየ ኣብርሃ

ሰሞኑን ኢሕአዴግ እና ሌሎች ሦስት ፓርቲዎች አንድ የጋራ ስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፣ በብዙኀን መገናኛም ሲጨባበጡ ታይተዋል:: የተፈራረሙበት ሰነድ *«የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ እና በደንቡ ማስፈጸሚያ መምሪያ ላይ ባደረጉት ድርድር ስምምነት የተደረሰበት ሰነድ»* ይሉታል:: የመጨባበጥ ድራማውን ተከትሎ የተደበላለቁ ስሜቶች እና አስተያየቶች ተንጸባርቀዋል::

የአቶ መለስ እና የአቶ ኀይሉ መጨባበጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሲኾን የአቶ ኀይሉ እና የአቶ ልደቱ አለመጨባበጥ ግን ምንም አልተባለለትም:: ይህም ኾኖ የመንግሥት ብዙኀን መገናኛዎች ይህ ክሥተት ታሪካዊ ርምጃ እንደ ኾነ ሊያሳምኑን እና ሊቀሰቅሱን እየሞከሩ ናቸው:: ማጠናከርያ ይኾንላቸው ዘንድ አንዳንድ የውጭ አገሮች አምባሳደሮችን ጠየቅን በሚል ምላሻቸውን እያስነበቡን ሲኾን በተለይ የአንዳንድ አምባሳደሮች ፎቶ ግራፎች ከመንግሥት ጋዜጦች የፊት ገጽ እንደተተከለ ሰንብቷል:: የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ነገሩን ደገፉት ለማለትም *«አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች»* የሚሉትንም እያሰሙን ነው:: መድረክ ስምምነቱን ባለመፈረሙ እየተዘመተበት ለመኾኑ እየወጡ ከሚገኙት ዘገባዎች ለመገንዘብ ይቻላል:: አራቱ ተፈራራሚ ሰዎች በኢትዮጵያ «ፖለቲካዊ ገበያ» የሚታወቁ ሰዎች እንደ መኾናቸው ነገ ይኖረናል ስለሚሉን ሥነ ምግባራቸው እንድንገምት የቆየ የፖለቲካ ጨዋታ ሥነ ምግባራቸውን ሳንመለከት አናልፍም::

## የቆየው የ«ሥነ ምግባር» ማኀደር

ከተፈራራሚዎቹ ውስጥ ሦስቱ የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነት ለዴሞክራሲ ሰዎች ናቸው:: የዚያ ዘመኑ ቅንጅት ለብዙ ኢትዮጵያውያን የታላቅ ተስፋ ምልክት የነበረውን ያህል ለኢሕአዴግ ደግሞ የታላቅ ስጋት ምልክት ኾኖ እንደ ነበር ይታወሳል:: የአቶ ኀይሉ ቅንጅት ታላቅ የሥልጣን ተቀናቃኝ የነበረ ጊዜ ኢንተርሃምዌ የሚል ስም ተለጥፎበት *«ታግለን እና ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለን ያስወገድነውን ሥርዐት መልሰው ሊጭኑብኝ ነው»* እየተባለ በእርሳቸው እና በፓርቲያቸው ላይ ከፍተኛ ቅስቀሳ መካሄዱም ይታወሳል::

አቶ ኀይሉ ከእነ ባልደረቦቻቸው የታሰሩ ሰሞን የኢሕአዴግ ሰይፍ መመዘዙን ያዩት አቶ ልደቱ ያ ሁሉ «ፀረ ወያኔ» ቅስቀሳቸው ቀረና ተጠቅልለው ወደ ኢሕአዴግ ጉያ ከመግባት አልፈው ታፍሰው እስር ቤት የገቡትን የገዛ ጓደኞቻቸውን መርገም እና ማውገዝ ጀመሩ:: ቅንጅት እንዲፈርስ ሲደረግ አቶ ልደቱ የሚች ንብረት የመካፈል መብት ተከብሮላቸው ሁለቱን ጣት ሲሸለሙ እዚህ ነበሩ የማይባሉት አቶ አየለ ጫሚሶ

ደግሞ ቅንጅት የሚለው ስም ተሰጣቸውና ባለፓርቲ ኾኑ:: አቶ ልደቱ ቀደም ብለው እንዳደረጉት ሁሉ ኢንጂነሩም ከእስር እንደተፈቱ የቀድሞ ፓርቲያቸውን ይዘው *«ወደ ፖለቲካ ተመልሻለኹ»* አሉ::

የምርጫ 97 የሕዝብ ትግል ለምት እና ለሽንፈት ለመዳረጉ፣ እነዚህ ሦስት ሰዎች እና አራተኛው ተፈራራሚ አቶ መለስ የነበራቸው ሚና እና አሁን ደግሞ አንድም ሦስትም ኾነው ለመምጣታቸው ምክንያቱ እንዲሁም የአራቱ ሰዎች የፖለቲካ ጨዋታ ሥነ ምግባር ምን እንደሚመስል እየታወቀ ይህን አሳምሮ ለሚረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ርምጃ ተፈጸመ በሚል በመንግሥት ብዙኀን መገናኛ እየተደረገ ያለው ውትወታ አንባቢውን፣ አድማጩን እና ተመልካቹን ለማሳመን ያዳግተዋል::

አሁን የምንገኘው 2002 ዓ.ም ላይ ነው፤ የኀይል ሚዛኑ በእጅጉ ተቀይሯል:: እነዚህ ሦስት ሰዎች ሦስት ፓርቲ(ለዚያውም ሰላም የማይባባሉ) ኾነው ከመምጣታቸውም ባሻገር ሦስቱም ተደምረው የቀድሞውን ቅንጅት የሚቀራረብ ኀይል የላቸውም:: ኢሕአዴግም ስጋት አይኾኑበትምና ከእነርሱው መተቃቀፉን መርጧል::

የሰነዱን መፈረም ተከትሎ «አቶ ኀይሉ እና አቶ መለስ እንዴት ሊስማሙ ቻሉ? አቶ ኀይሉ እንዴት ከአቶ ልደቱ እና ከአቶ አየለ ጫሚሶ ጋራ በአንድ ላይ ለመቀመጥ እና ለመስማማት በቁ?» የሚሉ ጥያቄዎች መነሣታቸው አልቀረም:: እዚህ ላይ ቁም ነገሩ የፍቅር ወይም የጥላቻ ጉዳይ አይደለም:: ቁም ነገሩ ያለው ካለንበት የፖለቲካ ትግል ምዕራፍ እና እርሱ ባስከተለው የኀይል ሚዛን ትንተና ላይ ነው፤ የሰሞኑን ክሥተት የፈጠረውም ይህ ስሌት ነው:: ዛሬ ለመጻፍ የፈለግኹትም በዚህ ጉዳይ ላይ ነው::

## የፖለቲካው ስሌት እና ስልት ለውጥ

በፈላስፎች ዘንድ *«አንዳንዴ ታሪክ ራሱን ይደግማል»* የሚል የተለመደ ብሂል አለ:: ይኸውም *«ቀደም ብለው የታዩት ክሥተቶች ተመልሰው የመጡ እስከሚመስሉ ድረስ አሁን ላይ ይታያሉ፤ ተዋናዮቹ ሳይቀር ተመሳሳይ ይኾናሉ ወይም ተመሳሳይ ስም ይዘው ብቅ ይላሉ፤ የቀደሙ ትዝታዎችንም ይቀሰቀሳሉ»* ይላሉ:: ይህ ሲኾን ታዲያ አዲስ ገቢው ወቅት ትላንት ከነበረው እና ታሪክ ከተሻገረው ወቅት የተለየ መኾኑን መገንዘብ እና ጠንቅቆ ማንበብ አስፈላጊ እንደ ኾነ አበክረው ያስገነዝባሉ:: *«ላይ ላዩን መመሳሰል ያለ ቢመስልም ቀድሞ የነበረው የፖለቲካ ኀይሎች አሰላለፍ መለወጡን እና ተመልሰው የመጡ የሚመስሉት ተዋናዮችም ከበስተጀርባቸው የሚያሰልፏቸው ኀይሎች የፊተኞቹ አለመኾናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል»* ይላሉ ፈላስፎች::

ለዚህ እንደ ጥሩ ምሳሌ የሚቀርቡት በፈረንሳይ ታሪክ የታዩት ሁለት ታሪካዊ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች እና በእነዚህ ወቅቶች ብቅ ያሉት ሁለት ናፖልዮኖች ተብለው የሚጠሩ መሪዎች ናቸው:: የመጀመርያው የፈረንሳይ የሕዝብ እንቅስቃሴ በ1789 የተከሠተው እና በተለምዶ «የፈረንሳይ አብዮት» ተብሎ የሚጠራው ሲኾን ሁለተኛው የሕዝብ እንቅስቃሴ

ደግሞ በ1848 ላይ የታየው ነበር። ከመጀመርያው የሕዝብ እንቅስቃሴ ጋራ በተያያዘ ወደ መሪነት ብቅ ያለው ስመ ጥሩው የጦር መሪ ናፖልዮን ቦናፓርት ሲኾን በሁለተኛው ላይ የታየው ግን የእርሱ ዘመድ የኾነው፣ ሉዊ ናፖልዮን የሚባለው፣ ፈረንሳይን ለጥፋት እና ለታላቅ የጦር ሜዳ ውርደት የዳረገ መሪ ነው።

በሁለቱም ወቅት የሕዝብ እንቅስቃሴ ነበር። በሁለቱም ወቅት ተመሳሳይ ስሞች የያዙ ሰዎች ብቅ ብለዋል። በሁለቱም ወቅቶች ግን ከእነዚህ ሰዎች በስተጀርባ የነበረው የፖለቲካ አሰላለፍ የተለያየ ነበር። በሁለቱም የሕዝብ እንቅስቃሴዎች መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥ በርካታ ኹኔታዎች ተለውጠዋልና ሁለቱ ናፖልዮኖች በፈረንሳይ ታሪክ የነበራቸው ስፍራም የተለያየ እንዲኾን ግድ ኾኗል። ስሞች እና ሰዎች ተመልሰው ቢመጡም የሚይዙት ተልእኮ የተለያየ ከመኾን አልፎ ተፃራሪም ሊኾን ይችላል። የስምን መደጋገም እና የትዕይንቶችን መመሳሰል ከበስተጀርባ ካለው የኀይል አሰላለፍ እና ሚዛን ነጥለው ከተመለከቱት ያሳስታል።

*«የጎሳ ድርጅቶች ስብስብ ነው»* በሚል መድረክን አልቀላቀልም ያሉት አቶ ኀይሉ ሻውል በአንድ ወቅት የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት(መአሕድ) መሪ ነበሩ። መአሕድ እንደ እኔ እምነት የብሔር ድርጅት እንደ አቶ ኀይሉ እምነት ደግሞ የጎሳ ድርጅት ለመኾኑ የሚያከራክር አይደለም። ኋላ ላይ ፓርቲያቸው መአሕድ ይህን ስሙን ቀይሮ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(መኢአድ) መባሉ ይታወቃል። አቶ ኀይሉ ለኢትዮጵያ አንድነት መጨነቃቸውን የማከብርላቸው ብኾንም ይህ እምነታቸው በብሔር ድርጅት (መአሕድ) እያሉ እንዳልተቀነሰ ሁሉ ፓርቲያቸውን ወደ ኅብረ ብሔር ድርጅት (መኢአድ) ሲቀይሩም እንዳልጨመረ መገንዘብ ግን አስፈላጊ ይመስለኛል።

መአሕድን ወደ መኢአድ መቀየራቸውን ተከትሎ አቶ ኀይሉ ከእነ አቶ ልደቱ እና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋራ በመኾን ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲን መሥርተዋል። የሚመሰገን ታሪካዊ ርምጃ ነበር። አቶ ኀይሉ ሊቀ መንበር፣ አቶ ልደቱ እና ዶ/ር ብርሃኑ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር በመኾን በምርጫ 97 ላይ የፈጠሩት ከፍተኛ የለውጥ እንቅስቃሴ በአክብሮት የሚዘከር ኾኖ ኋላ ላይ የኾነው ደግሞ በኀዘን እና በቁጭት የሚታወስ ይኾናል።

ዛሬ አቶ መለስ፣ አቶ ኀይሉ እና አቶ ልደቱ ቢኖሩም ያ የምርጫ 97 የሕዝብ እንቅስቃሴ እና ተስፋ ግን አሁን ከእነርሱ ጋራ የለም። ሦስቱም ከዚያው የምርጫ 97 ተስፋ ጋራ መያያዛቸው እንዳልቀረ ሁሉ ሦስቱም ከተስፋው መጥፋት ጋራ መያያዛቸውም አልቀረም። ዛሬ በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ ብንኾንም በምርጫ 97 ዋዜማ ላይ በነበርንበት ኹኔታ ላይ ግን አይደለንም። እነርሱ ዛሬ ድረስ ቢገኙም የዚያን ጊዜው ተስፋ እና ኀይል ግን ከእነርሱ ጋራ የለም።

በሌሎቹ ፖለቲከኞች ዘንድ የነበረውን እና እየኾነ ያለውን ደግሞ እንመልከት:: ፕሮፌሰር በየነ እና ፕሮፌሰር መረራ የሚመሩት ሌላ ጥምረት ነበር:: ምርጫ 97 ላይ ጥምረታቸውን ይዘው ተንቀሳቅሰው ታላቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ድምፅ እንደተሰረቀባቸው ቢያምኑም *«ውጤቱን ተቀብለን ለሚቀጥለው ምርጫ እንዘጋጃለን እንጂ ወንበራችንን አንለቅም»* ብለው ፓርላማ የገቡ፣ በዚህም ስንት ዘለፋ የደረሰባቸው ናቸው:: አልተካካዱም፤ እርስ በርስ አልተዘላለፉም፤ አሁንም በጋራ እየሠሩ ናቸው:: ይህን ሥነ ምግባር ልብ ይሏል::

አሁን ላይ ስንመጣ ደግሞ ስምንት ፓርቲዎች የታቀፉበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ተመሥርቷል:: አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው እና አቶ ገብሩ ዐሥራት ከእነ ፕሮፌሰር መረራ እና ፕሮፌሰር በየነ ጋራ በአንድ መድረክ ቁጭ ብለዋል:: የአደረጃጀታቸው ድንበር ሳይለያቸው የ«ጎሳ»፣ የ«ነፍጠኛ» ድርጅት የሚለውን ቅጽል መለጣጠፍ ተሻግረው እና ሁሉም ለኢትዮጵያ አንድነት እኩል የሚጨነቁ መኾናቸውን ተገንዝበው በጋራ ፕሮግራም በጋራ ምልክት ለመወዳደር እና የአንድነት መንግሥት ለማቋቋም ተስማምተው ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛሉ:: ይህ ክሥተት ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ ተስፋ መፈንጠቁም አንድ እና ሁለት የለውም::

ኢሕአዴግን መሀል ላይ እናስቀምጥና አቶ ኀይሉንም የያዘውን *«የቅንጅት ነበር»* ስብስብን እና መድረክን ከግራ እና ከቀኝ አስቀምጠን ብንመለከት ከዚህ ሊመጣ የሚችለውን የፖለቲካ ስሌት እና ስልት ለመገመት አይከብድም ብዬ እገምታለኹ:: መድረክ ከያዘው ስብስብ እና ካለበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከሠራው የቤት ሥራ አኳያ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ሰፊ ድጋፍ ሊያሰባስብ የሚችል ኀይል ነው:: በምርጫ 97 በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ የተፈጠረውን ቁስል የማሻር ዕድል ለመፍጠር፣ በዚህም በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር የሚችል ኀይል ነው:: ይህ ኀይል ለአራቱም ድርጅቶች ቀላል ያልኾነ ስጋት ከመኾኑ አኳያ በመሃላቸው የነበረውን ቁርሾ እናቆይ ቢሉ የኀይል ሚዛን ለውጥ የፈጠረው አስገዳጅ ኹኔታ ከመኾን ያለፈ ምክንያት ሊኖረው አይችልም::

በምርጫ 2002 የአቶ መለስን ሥልጣን ይገዳደራል ተብሎ የሚጠበቀው መድረክ በመኾኑ ከእንግዲህ የምት እና የውግዘት ባለተራው እርሱ እንጂ «ቅንጅቶቹ» ሊኾኑ አይችሉም:: እነርሱ ምናልባት ኢሕአዴግን ይገዳደራል የሚባለውን ኀይል በማዳከም ረገድ ይተባበሩ እንደ ኾነ እንጂ የኢሕአዴግን ሥልጣን በፍጹም ስጋት ላይ የሚጥሉ አይኾኑም:: በተለይ ሁለቱ ደግሞ በተባባሪነት እንጂ በተቃዋሚነት የሚጠረጠሩ አይደሉም:: የኢሕአዴግ የኀይል ሚዛን ስሌት እና ሰሞኑን ትልቅ ሽፋን የተሰጠው የሽራተኑ የእጅ መጨባበጥ ድራማ ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው::

## <u>መድረክ - የምት እና የውግዘት ተረኛ</u>

ኢሕአዴግ በምንም ተኣምር ከሚገዳደረው ጋራ መቀመጥ አይፈልግም:: የሚገዳደረውን ኀይል የተለያየ ስም እየለጠፈ እና በጠላትነት እየፈረጀ በጭራቅነት እንዲታይ በማድረግ ያጠፋዋል:: በምርጫ 97 በቅንጅቱ ላይ የደረሰው ይኸው ነው:: አቶ ልደቱ ሰይፍ ሲመዘዝ ወዲያውኑ ቀኝ ኋላ ዙር አደረጉ፤ ኢንጂነር ኀይሉ ሻውል ግን ቅልቅሉን «ወግ» ባለው መልኩ አሁን እንዲኾን አደረጉት:: ሁለቱም ሰዎች የወሰዱት ርምጃ ግን የይዘት ልዩነት የለውም::

ጠንካራ ተገዳዳሪ ይኾናል የሚባለው መድረክ ነው:: እርሱ በድርድሩ አካል እንዲኾን አልተፈለገምና *አይመቹ የኾነ* የድርድር አቋም ካልተቀበልኽ ተባለ:: አይኾንም ብሎ አቋሙን ከገለጸበት ጊዜ ጀምሮ የፕሮፓጋንዳ መአት ይወርድበት ጀምሯል:: ከአሁኑ ለዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ ምርጫ አሻፈረኝ አለ እየተባለ እየተቀሰቀሰበት ነው፤ እነ አቶ መለስ፣ አቶ አየለ እና አቶ ልደቱ እየተቀባበሉ «ፀረ ዴሞክራቲክ» እያሉት ነው:: ከፊርማ ሥነ ሥርዐቱ ወዲህ አቶ ኀይሉም ወደዚህ እየተሳቡ ነው:: በተለይ ሦስቱ ምኞታቸው እና ጸሎታቸው መድረክን በዐመፀኝነት የሚወነጅሉበት ሰበብ መፈለግ የኾነ አስመስሎባቸዋል - በቅንጅት ላይ እንደተደረገው::

ምርጫ 97 «እንከን የለሽ» መኾኑ ቀርቶ ሁከት በሁከት እንዲኾን ያደረጉት እነዚያ ሽራተን ሲጨባበጡ ያየናቸው ወገኖች እንጂ መድረክ ውስጥ ያሉት አለመኾናቸው እየታወቀ መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዳልቆመ መናገራቸው አስገራሚ ነው:: መድረክ እነርሱ ሲራገጡ የተበላሸውን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለመጠገን እየተንቀሳቀሰ ያለ ድርጅት ነው:: እነርሱ ጎሰኛ፣ ነፍጠኛ እያሉ ሲናቆሩበት የቆየውን የፖለቲካ ፍረጃ ተሻግሮ *«በኅብረ ብሔራዊ ይኹን በብሔራዊ ድርጅት ያሉት ሁሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው»* ብሎ የተነሣና በልዩነት ተሸፍኖ የቆየውን አንድነት ጎልቶ እንዲወጣ እያደረገ ያለ አዲስ የአብሮነት እና የመቻቻል ጥምረት ነው:: የነገው ተስፋ መድረክ እንጂ እነርሱ አይደሉም::

ኢሕአዴግ ከአቶ ልደቱ እና ከአቶ አየለ ጋራ «ተደራድሮ» *«በምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ከተቃዋሚዎቹ ጋራ ስምምነት ላይ ደርሻለኹ»* ቢል እነዚያ *«ኢሕአዴግ ሥልጣኑን ለማስቀጠል የቻለው በነጻ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስላሸነፈ ነው»* የሚል ምስክርነት ለመስጠት የቸኮሉት የውጭ አገር ዲፕሎማቶች ሳይቀሩ ሊቀበሉት ይቸግራቸዋል:: አቶ ኀይሉ የእነ አቶ አየለን እና አቶ ልደቱን አውቶቡስ በመሳፈራቸው ግን ለኢሕአዴግም ለዲፕሎማቶቹም ሸክሙን በተወሰነ ደረጃም ቢኾን አቅልለውላቸዋል::

ኢሕአዴግ ከጅምሩ ስለ ድርድር ሲያቅድ የድርድሩን አድማስ በሥነ ምግባር ዙሪያ ብቻ እንዲወሰን እንደ አንድ ግብ ይዞ ተነሥቷል:: መድረክ ምርጫው ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ ይኾን ዘንድ ከሥነ ምግባር ደንብ በተጨማሪ መነሣት ያለባቸውን አጀንዳዎች

ዝርዝር ይዞ ነበር የቀረበው፡፡ መድረክ ያቀረበው ሐሳብ የኢሕአዴግን ግብ የሚያፋልስ በመኾኑ ለኢሕአዴግ መድረክን መገፍተር ግድ የኾነውን ያህል አቶ ኀይሉን እንደምንም ብሎ በድርድሩ ማቆየትም ግድ ነበር፡፡ ይህ ባይኾን ግና ኢሕአዴግ ከገዛ ራሱ ተደራድሮ ከገዛ ራሱ ተፈራረመ ሊባል ነው፡፡ አቶ ኀይሉ ለሽፋን ሰጪነት ይፈለጋሉ፤ ፈረንጆቹም ይህን ይፈልጉታል፡፡ ለዚህ ዋጋ ይኾን ዘንድ አቶ መለስ ባይወደውም ራሱ መጥቶ መፈረሙ እና መጨባበጡ አይቀሬ ነበር፡፡

## <u>ትርፍ እና ኪሳራ</u>

ከዚህ ስምምነት ተብዬ ነገር ኢሕአዴግ እና አቶ መለስ ያተርፋሉ፣ ኢንጂነሩም የሚያተርፉት ነገር ይኖራል፡፡ አቶ ኀይሉ ከምርጫ 97 ወዲህ የነበራቸው ኀይል እና ተሰሚነት እምብዛም ነው፡፡ ያ ሁሉ የሕዝብ እንቅስቃሴ እና የሕዝብ ተስፋ እርሳቸው ይመሩት የነበረው ፓርቲ ባሳየው የአመራር ጉድለት መና ቀርቷል፡፡ እርሳቸው እና ጓደኞቻቸው ከእስር ሲፈቱ ያ የቅንጅት ደጋፊ እና አባል በመኾን መከራውን ያየው፣ ከእስር እንዲፈቱለትም የጠየቀው ሕዝብ የጠበቀው ሰዎቹ ተባብረው ትግሉ የሚያንሠራራበትን አመራር እንዲሰጡ የነበረ ቢኾንም በተጨባጭ የኾነው ግን ሌላ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ በእርሳቸው ተስፋ ሳይቆርጥ አልቀረም ማለት አይቻልም፡፡

መድረክ ተገፍትሮ በወጣበት ኹኔታ አቶ ኀይሉ ከአቶ አየለ እና ከአቶ ልደቱ «ተቃዋሚነት» ረድፍ ራሳቸውን አሰልፈው ከኢሕአዴግ ጋራ መቀራረባቸው እና ተደራደርኹ ማለታቸው *«ለሌሎች የተዘጋው በር ለእኔ ተከፍቶ ፓርቲዬ እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ ዕድል ያገኛል፤ ከዚህም ለምርጫ 2002 ከሌሎቹ የተሻለ ዝግጅት አድርጌ እነርሱ ከሚያገኙት የተሻለ ወንበር አገኛለኹ»* የሚል ስሌት ሳይኖራቸው አይቀርም፡፡

ራሱን እንደ ቁርጥ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ የሚያስብ ፖለቲከኛ ለሁሉም ተቃዋሚዎች ሊጠበቅላቸው የሚገባውን ሕገ መንግሥታዊ መብት ይጠበቅ ዘንድ ይጠይቃል፤ ይታገላል እንጂ ከገዢዎች ጋራ በመሞዳሞድ ለሌሎች የተከለከሉትን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች በልዩ ኹኔታ በማግኘት ከሌሎች በልጬ እገኛለኹ፡፡ በዚህም እቀድማለኹ ብሎ ማሰብ ጨዋ የፖለቲካ ጫዎታ ሥነ ምግባር አይደለም፡፡

ፖለቲካ የአገር እና የሕዝብ ጉዳይ ነው፤ በፖለቲካ የሚገኝ ስኬትም በሕዝብ ከመታመን የሚመነጭ እንጂ በእንዲህ ዐይነት ስሌት የሚገኝ አይደለም፡፡ ለዚህማ ቢኾን እነ አቶ ልደቱ ምርጫ 97ን ተከትሎ የፈጸሙት አስገራሚ የፖለቲካ አክሮባት እንደምን ስሕተት ነው ብሎ መተቸት ይቻላል፡፡ አቶ ልደቱን ለይተው ከጭብብጡ ማውጣታቸው ተገቢ ነው ባልልም ለዚህ ለዚህማ ከኾነ ኢንጅነሩ አቶ ልደቱን ለመጨበጥ ከመከልከል አልፈው እቅፍ አድርገው ሊስሟቸው በተገባ ነበር፡፡

ኢሕአዴግም የሚያገኘው ጥቅም አለ:: በዚህ የዕቅዱ የመጀመርያው ምዕራፍ ሊባል በሚችል ድርጊቱ መድረክን የመግፋት እና አቶ ጎይሉን በድርድሩ የመያዝ ግቦችን አሳክቷል:: ከዚህ ሊያገኝ የፈለገው ጥቅም በዋናነት *«ይኸውላችሁ ምርጫ 2002 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ይኸን ዘንድ ከተቃዋሚዎች ጋራ እየተደራደርኹ ነው»* ብሎ የውጭ መንግሥታትን ማሳመን ነው:: ስምምነቱ የተፈረመበት ቀለም ሳይደርቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሥዩም መስፍን ወደ ዋሽንግተን ሄዶ ከአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሴክሬታሪ ወ/ሮ ሂላሪ ክሊንተን ጋራ መገናኘቱ፣ በዚሁ ፊርማ ላይም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መነጋገሩ የሚያመለክተውም ይህንኑ እውነታ ነው:: የቀደመ ምኞታቸው መድረክ በዚህ ጉዳይ ተሳትፎ መፈራረሙ ነሐሴ ላይ አልቆ አቶ መለስ ለተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ወደ ኒው ዮርክ ሲሄድ ይህን ድል ይዞ እንዲሄድ የነበረ ይመስለኛል:: ነገሩ ያልተሳካው መድረክ ይህን ድል ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመኾኑ ሳይኾን ኢሕአዴግ ለመቀበል እንጂ ለመስጠት ዝግጁ ኾኖ ባለመቅረቡ ነበር::

## <u>መጨባበጡ ያከሰማቸው ክሦች</u>

አቶ ጎይሉ እና አቶ መለስ ለመጨባበጣቸው ዋናው ምክንያት እያንዳንዳቸው እናገኝ ዋለን ብለው ካሰቡት ጥቅም የመነጨ ቢኾንም መጨባበጡ በራሱ እነርሱ ያልጠበቁት አንድ በጎ አንደምታ ሊኖረው ይችላል የሚል እምነት አለኝ:: ይኸውም ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ተቃዋሚዎችን በኢንተርሃምዌነት ከመክሰሱም ባሻገር በአቶ ጎይሉ መአሕድነት በኩል እየገባ ቅንጅትን በነፍጠኝነት ሲከስ፣ ቅንጅት ለሥልጣን ከመጣ የትግራይ ተወላጆችን *«እንደ ሐውዜን ዐይነቱ የዘመነ ደርግ ግፍ ይመጣባችኋል»* ሲል በኦሮሚያ ክልል ደግሞ *«የነፍጠኛው ሥርዐት ተመልሶ ይመጣባችኋል:: እነዚህ ከሚመጡባችኹ እኔ እሻላችኋለኹ»* ሲል ቀስቅሷል::

ቅስቀሳው ትክክለኛ ስልት ባይኾንም አልሠራም ለማለት አይቻልም:: በቴሌቪዥን በተለይ በእነ አቶ ልደቱ ሲሰጥ የነበረው ቅስቀሳ ደግሞ ትግራይን በልዩ ተጠቃሚነት በመፈረጅ የትግራይ ተወላጆችን ስጋት ላይ የሚጥል ነበር:: በየቀበሌው የነበረው ቅስቀሳ ደግሞ ከዚህ የባሰ እንደ ነበረ እና በዚህም በትግራይ ተወላጆች ላይ ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሮ እንደ ነበር ለመገንዘብ ችያለኹ::

አቶ መለስ እና አቶ ጎይሉ ሻውል የዚህ ጽንፍ የረገጠ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አመለካከት እና መናቆር አቀንቃኝ የኾኑ ፓርቲዎች መሪዎች በመኾናቸው የሁለቱ መጨባበጥ የዚህ አመለካከታቸው መሸነፍ እና መክሰር ብሥራት ሊኾን ይችላል:: የኢትዮጵያውያን በጎሪጥ የመተያየታቸው ጉዞ ማብቂያው ምዕራፍ ላይ ለመድረሱ ምልክት ሊኾን ይችላል::

አቶ ገብሩ ዐሥራት በመስቀል አደባባይ በተጠራው እና እነ አቶ ጎይሉ ሻውል በተሳተፉበት ሕዝባዊ ስብሰባ መገኘቱ እንደ ክሕደት ተቆጥሮ ትግራይ ውስጥ

«ከጠላቶቻችን ጋራ አበረ» ተብሎ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ተካሂዶበታል፡፡ አሁንም ዓረና *«ትግርኛ ተናጋሪ ቅንጅት»* የሚል ስም በህወሓት የፕሮፓጋንዳ መሪዎች በኾኑት በእነ አቶ ቴዎድሮስ ሐጎስ ወጥቶለታል፡፡ ይህ መጨባበጥ የህወሐት የፕሮፓጋንዳ መሪዎችን እና ካድሬዎችን አፍ አስይዞ በዓረና እና በህወሓት መካከል የሚኖረው ልዩነት በቁም ነገር ላይ ያተኮረ እንዲኾንም ይረዳ ይኾናል፡፡

## የልዩ መብት እስረኛው

ኢሕአዴግ አቶ ኀይሉን በእጁ ካስገባ እና መድረክን ከገፈተረ በኋላ የሚቀጥለው ዕቅዱ አንድ ልዩ ክበብ በመፍጠር አቶ ኀይሉን በዚሁ ክበብ ማሰር፣ መድረክን ደግሞ ከዚሁ ክበብ ውጭ አድርጎ ትግሉ በሁለቱ ቡድኖች መካከል እንዲኾን ማድረግ ይመስላል፡፡ አቶ ኀይሉን አሁን በሰንሰለት ባያስራቸውም ልዩ መብት የሚያስገኝ ክበብ አባል እንዲኾኑ እና ጥቅም የሚያስጥ ግዴታ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ እንዲታሰሩ አድርጓቸዋል፡፡ ይህን እንመልከት፡፡

*ኢንተርናሽናል አይዲያስ* የሚባለው የስዊድን ተቋም ያዘጋጀው የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ ምግባር ደንብ የሥልጣን ብልግናን ወይም ሙስናን ይጠየፋል፤ የተዘጋጀውም ከሙስና የጸዳ ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ ምርጫ ይካሄድ ዘንድ በፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ውድድር ዓለም አቀፍ የፉክክር ሥነ ምግባር ደረጃን የጠበቀ እንዲኾን ለማድረግ ነው፡፡ ተቋሙ ከፓርቲዎች የውድድር ሥነ ምግባር በተጨማሪ የምርጫ አስተዳደር እና የምርጫ ታዛቢዎች ሥራ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ይኾኑ ዘንድ ሁለት የሥነ ምግባር ደንቦችን አዘጋጅተዋል፡፡ መድረክ በፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ይዘት መሠረታዊ ችግር እንደሌለበት ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ ለእንግሊዝ አምባሳደር እና ለባልደረቦቻቸው አሳውቋል፡፡ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ እንደ ቅቡል የሚወስድበት አግባብ*(context)* እንዳለ በመገንዘብ፣ ይህ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ኹኔታ የሌለ መኾኑን በማስተዋል፣ ይህ ጠገግ ይኖር ዘንድ መነሣት ያለባቸው ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉና እነርሱም በአጀንዳነት እንዲካተቱ ነበር አቋሙ፤ አጀንዳዎቹም የቀረቡ ሲኾን የምርጫ አስተዳደሩ ተአማኒነት፣ ገለልተኛነት እና የምርጫ ታዛቢዎች ጉዳይ ከቀረቡት ዝርዝር ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ኢሕአዴግ ለመቀበል እንጂ ለመስጠት ዝግጁ ባለመኾኑ ይህ ሐሳብ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አራቱ ተዳዳሪዎች ሦስት ሰነዶችን ነው ያወጡት፡፡ አንዱ አጠቃላይ የስምምነት ሰነድ ኾኖ የአራቱም ፊርማ ያረፈበት ነው፡፡ ሁለተኛው የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ሲኾን ሦስተኛው ደግሞ የምርጫ ሥነ ምግባር ደንቡን በሥራ ላይ ለማዋል የተዘጋጀ መመሪያ ናቸው፡፡

በመጀመርያው እና ፊርማቸውን ባሳረፉበት ሰነድ አንቀጽ 12፣ *«ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጎማ በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስምምነት መሠረት ለሁሉም*

*ተወዳዳሪ ፓርቲዎች»* እንደሚከፋፈል ተመልክቷል፡፡ ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት የተባለው ፍጥረት በተፈራራሚ ፓርቲዎች እንደሚቋቋም በሥነ ምግባር ደንቡ አንቀጽ 13 ላይ ተመልክቷል፤ በዚህም ተፈራራሚዎቹ ለማን ፓርቲ ምን ያህል ገንዘብ ይሰጠው የሚለውን ይወስናሉ ማለት ነው፡፡ በዚህም ተፈራራሚዎቹ ለራሳቸው ልዩ መብትን ሰጥተዋል፡፡ ደንቡን በሥራ ላይ ለማዋል በተዘጋጀው መመሪያ ይህ የተፈራራሚ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በምርጫ ሂደቱ ከተወዳዳሪ ፓርቲዎች በኩል የሚቀርብን አቤቱታ እና ቅሬታ አዳምጦ ውሳኔ እንደሚሰጥ ተመልክቷል፡፡

ይህ ነጥብ በምርጫው ነጻነት እና ተአማኒነት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ሳንካ በምሳሌ እንመልከት፡፡ መድረክ የዚህ ስምምነት ተፈራራሚ አይደለምና አንድነትም የዚህ ተፈራራሚ አይደለም፡፡ በዚህ ኹኔታ አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትሕ ፓርቲ በሰሜን ሸዋ በሚያደርገው ውድድር አራቱም ተፈራራሚዎች ከአንድነት ጋራ መወዳደር እንደሚችሉ እንገምት፤ አንድነት አቤቱታ ቢኖረው አራቱም ተከሳሽ እና ዳኛ ኾነው ሊቀመጡ ነው፡፡ እንዲህ ባለው ኹኔታ ነገሩ ሁሉ *«አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ»* አይኾንም ማለት አይቻልም፡፡ ወደ ገንዘብ ድልድል ሲመጣም ተፎካካሪዎቻቸውን ለማዳከም ሲሉ ገንዘቡን ሲቀንሱባቸው እነርሱ ጋራ ሲመጣ ግን *«ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ»* አያደርጉትም ለማለት ይከብዳል፡፡

በንግድ ሕጋችን ውስጥ የኩባንያ ምሥረታ ሐሳብ አፍላቂዎች እና መሥራቾች ልዩ ጥቅም እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡ የተፈራራሚዎች «ልዩ መብት እና ጥቅም» ከቢዝነስ ዓለም ወደ ፖለቲካ ዓለም መዝለቁ ግን አግራሞትን አጭሮብኛል፡፡ ከአገር እና ከመላ ኢትዮጵያውያን ነጻነት ጋራ የተያያዘን ምርጫን በሚያኽል ትልቅ ጉዳይ ላይ ለተፈራራሚዎች ልዩ መብት የሚሰጥ ነጥብ መስፈሩ በእጅጉ የሚያሳፍር ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ታላቅ ስድብ ነው፡፡ በዚህ የጀመሩት ሰዎች የጫዎታው ሥነ ምግባራቸው የት ድረስ ሊወስደን እንደሚችል ምልክቱ እያገኘን ያለ ይመስለኛል፡፡

የኢሕአዴግ የሕዝብ እና የውጭ ግንኙነት መምሪያ ሐላፊ አቶ ሴኩቱሬ ጌታቸው ከቪኦኤ ጋራ ባደረገው ቃለ ምልልስ መድረክ ስምምነቱን ከፈረመ የዚህ ተጠቃሚ ይኾናል ሲል አዳምጫለኹ፤ ካልፈረመ ግን የዚህ ተጠቃሚ አይኾንም ማለት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ የተለመደ *ማባበያን እና ቁንጠጣን ያጣመረ (carrot and stick)* የኢሕአዴግ ስልት መኾኑ ነው፡፡ ኢሕአዴግ ይህን ስልት በምርጫ ጉዳይ ማስገባቱ የፖለቲካን ክብር እና ዋጋ ምን ያህል እንዳወረደው የሚያመለክት ነው፤ ድምፅን በገንዘብ ከመግዛት፣ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ብሎ ኮሮጆ ከመገልበጥ ያልተናነሰ ወንጀል መኾኑ የተዘነጋ ይመስላል፡፡

በመሠረቱ አቶ ኀይሉ ከኢሕአዴግ ጋራ መደራደራቸው ስሕተት ነው አልልም፡፡ መድረክም ቢኾን እንደራደር እያለ ነው፡፡ ከኢሕአዴግ ጋራ መደራደር የሚመራበት

መርሕ ግን የምርጫ ሜዳውን ለሁሉም ወገኖች እኩል እና ነጻ በማድረግ ላይ መመሥረት አለበት:: መድረክ የጠየቀው እና ኢሕአዴግ ያልፈለገው ደግሞ ይህን ነው:: እርሳቸው አንድ ራስ፣ ኢሕአዴግ ግን ሦስት ራስ በኾኑበት አግላይ ምክር ቤት የሚያገኙት መብት *የተቸረ መብት* ከመኾን እንደማያልፍ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ይህን የተቸረ ልዩ መብት ለማግኘት የሌሎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የመጋፋት አደጋ ባለው ክበብ ውስጥ መግባታቸው በአጠፌታው በፓርቲያቸው እና በራሳቸው ተአማኒነት እና ስም ላይ ሊያጠላ የሚችለውን አደጋ ማጤን ያለባቸው ይመስለኛል::

## ከቧልት ያልዘለለው የዲፕሎማቶቹ ዲስኩር

በአዲስ አበባ ያሉ አንዳንድ ዲፕሎማቶች ይህን ስምምነት በማቀነባበር እና ነገሩ ኢሕአዴግ በቀየሰው መልኩ እንዲካሄድ በማድረግ ረገድ ብዙ ጥረት አድርገዋል:: መድረክ የራሱ አቋም ያለው ጥምረት ነው:: ኢሕአዴግ ካቀረበው የተለየ አካሄድ ሲያቀርብ ሁለቱንም የሚያቀራርብ አማካይ መንገድ በመፈለግ ፈንታ *«መንግሥት ይህን ስለማይቀበለው እርሱ ያለውን ተቀብላችኹ ሂዱ»* እስከ ማለት ድረስ ሄደዋል:: መድረክ ከዚህ ስምምነት ውጭ መኾኑን እያወቁ እና ለተፈራራሚዎች «ልዩ መብት» የሚሰጠው የስምምነቱ አንቀጽ በምርጫው ነጻነት እና ተአማኒነት ሊፈጥር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመገንዘብ እየቻሉ *«ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስምምነት ነው»* ብለው ምስክርነት መስጠታቸው በጣም የሚያስተዛዝብ ነው:: በመድረክ ደረጃ የሚገኙን ግዙፍ የተቃዋሚ ስብስብ አግልሎ ይህን ዐይነቱን ስምምነት መፈረም ምርጫ 2002ን ነጻ፣ ግልጽ እና ተአማኒ ያደርገዋል ማለት ከቧልት ያልዘለለ ዲስኩር ነው::

## *ቀውስን ማርገብ ወይስ ቀውስን ማስቀረት*?

የምርጫ 97 ጨዋታ እስከ ግንቦት ሰባት ማታ ደኅና ነበር፤ ጨዋታው መበላቱን ግልጽ ያደረገው የማታው የአቶ መለስ ልዩ መመሪያ እና እርሱን ተከትለው የመጡት ርምጃዎቹ ነበሩ:: የዓርብ ጥቅምት 20 ቀን 2002 የሸራተን ሆቴሉ ድራማ በምርጫ 97 ከታየው በተለየ ምርጫ 2002ን ጨዋታው ሳይጀመር በፊት የተበላ ያደረገው ይመስላል:: አቶ መለስ ይህን ዐውቀታል:: ፈረንጆቹ እና አቶ ኀይሉ ማወቃቸውን ለመገመት ግን እቸገራለኹ::

ነገሩ በዚህ ከቀጠለ ምርጫ 2002 በምርጫ 97 የተፈጠረውን ቁስል በማሻር ፈንታ እንዳያባብሰው እሰጋለኹ:: አገራችን በአሁኑ ወቅት ካለችበት አጠቃላይ ኹኔታ አንጻር ምርጫ 2002 መታየት ያለበት እገሌ ፓርቲ ከፓርላማ ወንበሮቹ ውስጥ ስንቱ ደረሰው ከሚል ስሌት የዘለለ መኾን ይኖርበታል:: ከዚሁ ያልተናነሱ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ችግሮች እንዳሉም መገንዘብ ይኖርብናል:: የአገሪቱን ቁርሾዎች በማርገብ የዜጎችን ሥነ ልቡና የማረጋጋት እና ውስጣዊ ሰላም የመፍጠር ተግዳሮት ባልተወጣንበት፣ በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንዲሉ ላለፉት ሁለት ዓመታት

ሲንከተከት የቆየው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሳይበቃ የሚልዮኖችን ሕይወት ለአደጋ የጣለው የ2002 ዓ.ም ችጋር ላይ በገባንበት እና የአካባቢያችን ጸጥታ አሁንም መልክ ባልያዘበት ኹኔታ ውስጥ መኖራችን መረሳት አይኖርበትም:: በምርጫ 2002 ከወዲሁ እየተደነቀረ ያለው ሳንካ አገራችን አሁን ባለችበት አሳሳቢ ኹኔታ ላይ ቢጨመር ሊከተል የሚችለው መዘዝ ቀላል ተደርጎ መታየት የለበትም::

ምርጫ 97 መደፍረሱ የታየው በመጨረሻው ሰዓት በመኾኑ፣ የተከተለውን አደጋ ለማስቀረት የነበረው ጊዜ ያን ያህል ውሱን በመኾኑ፣ ነገሮች ከእጅ ወደ አፍ በኾነ እና እጅጉን ድንጋጤ በተጫጫነው ስልት እንዲፈቱ ኾኗል:: አሁን ለምርጫ የቀረው አምስት ወራት ነው፤ ይህ ጊዜ ብዙ ባይኾንም ከምርጫ 97 በተነጻጻሪ ነገሩን ለማስተካከል አሁን የተሻለ ጊዜ እና ዕድል አለ:: አቶ ኀይሉም ኾነ አቶ መለስ ይህን ነገር ለማስተካከል ቆም ብለው ቢያስቡበት የተሻለ ይመስለኛል:: እዚህ ያሉት ዲፕሎማቶችም ስለዚህ አገር ፖለቲካ እነርሱ ከሚያውቁት በላይ ኢትዮጵያውያን እንደሚያውቁ ተገንዝበው የአንድ ወገን ድምፅ ብቻ አዳምጠው ተቀብሉ ብለው ወደ ጫና ከመሄድ በፊት ጆሯቸውን ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ጣል ቢያደርጉ ይበጃል::

በምርጫ 97 ቀውስ እንደ ተፈጠረ የፕሬዝዳንት ቡሽ አስተዳደር ወ/ሮ ቪኪ ሃድልስተንን በጉዳይ አስፈጻሚነት ደረጃ በመላክ *«ቀውስን የማርገብ»* ፖሊሲ ተግባራዊ አድርጓል:: ከወቅቱ ኹኔታ አኳያ «ቀውስ የማርገብ»ን ፖሊሲ መከተላቸው ስሕተት ባይኾንም ቀውሱን ለማርገብ የጣሩት የመንግሥትን ሥልጣን ለያዘው ወገን ባደላ መልኩ በመኾኑ ያኔ የተመረጠው ፖሊሲ ወደ ዛሬው በጎ የመሸጋገሪያ ድልድይ ሳይፈጥር ቀርቷል::

ለምርጫ 2002 አምስት ወር በቀረበት ኹኔታ እንደ መኖራችን ወቅቱ ግድ የሚለው ፖሊሲ «ቀውስን የማርገብ» ሳይኾን *«ቀውስን የማስቀረት»* ፖሊሲ ነው:: በመኾኑም ፕሬዝዳንት ኦባማ ሳይረፍድ በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል:: የፕሬዝዳንት ኦባማ መንግሥት የኢትዮጵያን ኹኔታ አስቀድሞ ሊመለከተው ከቻለ በኢትዮጵያ ከምርጫ 2002 ጋራ በተያያዘ ሊመጣ የሚችለውን ቀውስ የማስቀረት ዕድል አለው የሚል እምነት አለኝ::

እዚህ ካለው የእንግሊዝ ኤምባሲ እንቅስቃሴ ለመገንዘብ እንደቻልነው የጠቅላይ ሚኒስትር ጎርደን ብራውን መንግሥት ኢትዮጵያን በሚመለከት እየሠራበት ያለው የቡሽ አስተዳደር ወ/ሮ ቪኪን በመላክ ያከናወነው «ቀውስ የማርገብ» ፖሊሲ ይመስላል:: እነርሱንም አስተዋፅኦዋችኹን እናከብራለን እንላቸዋለን:: ፖሊሲያችኹ ግን «ቀውስን ማስቀረት» ይኹን፤ ያለንበት ወቅት ይህን ዕድል ለመጫወት ያስችላልና ሳይመሽ ቆም ብላችኹ ፖሊሲያችኹን ከልሱ እንላቸዋለን::

***አቶ ስየ ኣብርሃ፣ የመድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ መሥራች ናቸው:: ጸሐፊውን ለማግኘት የሚሹ በseabrag@gmail.com ሊጽፉላቸው ይችላሉ::**